# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter
Published by the Public Relations and Communication Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-7 ጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-7 October, 2017 G.C




በተማሪዎች የተሰራ የጋራ መፀዳጃ ቤት

- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የኤክስቴንሽን ተማሪዎች የህዝብ የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን አሰርተው ለተጠቃሚዎች አስረክበዋል፡፡
- መፀዳጃ ቤቶች ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን ሃሳብ ወደ ተግባር መቀየሩን ያሳየ ሲሆን የወደፊት ሥራቸው ላይ የሚኖረውን ሙያዊ ተግዳሮቶችና የሚፈቱበትን መንገድ አመላካች ነበር፡፡
- መፀዳጃ ቤቶቹ የተሰሩት በአየር ማረፊያና አካባቢው ለአሽከርካሪዎች፣ ለቆሎ ተማሪዎች ለግቢ ተማሪዎችና እንዲሁም በቀበሌ 03 ደግሞ ለገበያተኛው የጋራ መጠቀሚያ የሚሆኑ ናቸው፡፡
- መፀዳጃ ቤቶች የተሰሩት ከአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ከመንቆረር ኮንስትራክሽን፣ ከአልማና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡
- ይህ መሰል ተግባር በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ታቅፎ በስፋት ሊሰራበት እንደሚገባም ተገልጿል፡፡

## በውስጥ ገፆቻችን


- ለአዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ተደረገላቸው......... 1
- የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ምርጫ ተካሄደ.................3
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ መጽሐፍትን በልገሳ አገኘ ..........................5
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በፓናል ውይይት አከበረ................. 6
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ...........................7
- የግብርና ኮሌጅ ከጃፓይጐ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ስልጠና ሰጠ..................9
- የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ኤክስቴንሽን ተማሪዎች የጋራ መፀዳጃ ቤት ሰርተው አስረከቡ...10
- ለአዳዲስ መምህራን ስልጠና /Induction Training/ ተሰጠ....................12
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ሃገር አቀፍ ግምገማዊ ስልጠና አካሄደ............14
- በቡሬ ካምፓስ ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጠ............15
- Haddis Alemayehu Cultural Study Institute Conducts Proposal Defense ...............18
- Debre Markos University Establishes Partnership with Addis Ababa University ................19
- Debre Markos University has got books via Donation ......................20
- Debre Markos University College of Agriculture Gives Training in association withስ Jhpiego .......21

# ራዕይ
# Vision

እ.ኤ.አ. በ2025 ከአፍሪካ 10 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

**Debre Markos University strives to be one of the top ten Universties in Africa by 2025.**

# ተልዕኮ
# Mission

ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

**Producing competent, ethical and innovative graduates through providing quality instructional, Co-curricular and cultural involvement.**

አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

**Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders at local and national levels.**

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

**Providing demand driven community and consultancy services that contribute to the national development objectives.**

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት እየተዘጋጀች ለአንባብያን የምትደርሰው ወርሃዊ ዜና መጽሔት በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተካሄዱ የተለያዩ ሁነቶችን ዘገባ፣ የዩኒቨርሲቲውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ሌሎች ቁምነገሮችን አካታ ለንባብ ስትበቃ ቆይታለች፡፡

በዚህ እትም የጥቅምት ወር 2010 ዓ.ም. ዜና መጽሔታችን በዩኒቨርሲቲው የተደረጉ ውይይቶችን በስፋት ዳሳለች፡፡ መልካም ንባብ!

ለወርሃዊ ዜና መጽሔታችን መሻሻል የእናንተ የአንባቢያን አስተያየት ወሳኝ በመሆኑ ለሚኖራችሁ ማንኛውም አስተያየት

በድረ ገጽ www.dmu.edu.et ወይም

በኢ.ሜል dmu.cc2008@gmail.com አድርሡን!!

# ለአዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ተደረገላቸው

*ስማቸው አየነው*






የፕሮግራሙ ከፊል ገጽታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2010 ዓ.ም. ተመድበው ትምህርታቸውን ለመከታተል አዲስ ለገቡ ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው የሥርዓተ ፆታ፣ ኤች አይቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አዘጋጅነት የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ተደረገላቸው፡፡

በእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮግራሙ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ታደሠ ጤናው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሴቶችን በየደረጃው ለማብቃት ትኩረት ሠጥተው እየሠሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን የስርዓተ ፆታን፣ ኤች አይቪ ኤድስና አካል ጉዳተኞችን በሚመለከት በዳይሬክቶሬት



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ደረጃ በማቋቋምና በሥሩ ባለሙያዎችን በመመደብ እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ከቤተሠብና ከአካባቢያቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ርቀው የመጡ ሴት ተማሪዎችን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮች ተቋቁመው ውጤታማ ሆነው እንዲወጡ የማገዝ ስራ ይሠራል፡፡ እንዲሁም በአካዳሚክ ዘርፍ ዝቅተኛ ውጤት የሚያመጡ ሴት ተማሪዎችን የቱቶሪያል ፕሮግራም ቀጣይነት እንደሚኖረው አቶ ታደሠ ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ሴት ተማሪዎች እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች ከመጠቀም አንፃር ክፍተቶች ቢታዩም ክፍተቶችን በመቅረፍ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች በመቋቋም የመጡበትን አላማ ማሳካት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

በፕሮግራሙ ላይ በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ አንጋፋ ሴት መምህራን የህይወት ተሞክሯቸውን በማካፈል እንዲሁም በደብረ ማርቆስ ቤተሠብ መምሪያ የስነ ተዋልዶ ጤና የውይይት ጽሁፍ ቀርቦ ግንዛቤ የተፈጠረ ሲሆን የስርዓተ ፆታ፣ ኤች አይ ቪ/ ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ የውልሠው መላክ ሴት ተማሪዎችና አካል ጉዳተኞችን ለማገዝ ዳይሬክቶሬቱ ዝግጁ እንደሆነና በቀጣይም መሠል ፕሮግራሞች እንደሚያዘጋጁ ገልፀዋል፡፡

በፕሮግራሙ ከተገኙት መካከል የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ ይህ ፕሮግራም የተዘጋጀው ለሴት ተማሪዎች በወጣትነት እድሜ ደረጃ ስለሚገኙና ለአካባቢው አዲስ በመሆናቸው የሚደርሱባቸውን ልዩ ልዩ ችግሮችና ተጽዕኖዎች መቋቋም እንዲችሉ በማሠብ ስለሆነ ያገኙትን ግንዛቤ በመጠቀም ብቁና ተወዳዳሪ በመሆን ዓላማቸውን ማሳካት እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ምርጫ ተካሄደ

በእንደሻው ያዛቸው



የምርጫው ሂደት በከፊል

**ደ/ማ/ዩ፡-** አዲሱን የከፍተኛ ትምህርት አመራር ምደባ መሰረት በማድረግ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ምርጫ ተካሄደ፡፡ ምርጫው ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች ያደረገውን የውድድር ማስታወቂያ ጥሪ መሰረት እጩዎች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ፊት በማቅረብ የምርጫ ድምፅ አሰጣጥ እንዲሰጥ በማድረግ ነው፡፡

በምርጫው የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ዘርፍ አባላት፣ ከተማሪዎች፣ ከመምህራን ማህበር፣ ከአስተደደር ሰራተኞች የተውጣጡ ተወካዮችና እና የሴኔት አባላት በምርጫው ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ መራጮች የምክትል ፕሬዝዳንት ምርጫን አስመልክቶ ዕጩዎች ባደረጉት የምረጡኝ ቅስቀሳና ያስቀመጡትን አማራጭ የአመራር ስትራቴጂ ተከትሎ ነፃና ግልጽ የሆነ ምርጫ ጥቅምት 30/2010 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲው አዳራሽ መርጠዋል፡፡

የተወዳዳሪዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ እና የምርጫ ስነ-ስርዓቱን የመሩት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ ይልቃል ከፋለ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት ጊዜያትም የምክትል ፕሬዝዳንት ምርጫ በዚህ መሰል ሂደት ሲከተል



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡ አሁንም ይህ የደብረ ማርቆስ ተሞክሮ ያሳዪ የትምህርት ሚኒስትር መመሪያ የምርጫ ሂደቱም እጩ ተወዳዳሪዎችን በመመዝገብ ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የወከሉ የማህበረሰብ አካላት ለምርጫ እንደቀረቡም አቶ ይልቃል ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ከእጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ያቀረቡትን የቅስቀሳ ይዘት መሠረት አድርገው ቦታውን በእውቀትና በብቃት ሊመራ የሚችለውን ተወዳዳሪ ሚዛናዊ ሆነው እንዲመረጡ አቶ ይልቃል ለመራጮች መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በተጨማሪም መራጮች ነጥቦችን በትክክልና ከስርዝ ድልዝ ነፃ አድርገው ሊሞሉ የሚችሉበት መስፈርቶች በቅጽ በማዘጋጀት የትምህርት ደረጃ 25%፣ የስራ ልምድ 25%፣ ሴኔትና የማህበረሰብ ተወካይ ባሉበት የሚሰጥ ውጤት 30% እንዲሁም የተወዳዳሪዎች ባቀረቡት ሰነድ እና የውድድር ፅሁፍ (statement) በምርጫ ኮሚቴዎች 20 % ይዘው ነጥቡን ለቦርዱ በማቅረብ የመጨረሻው ውሳኔ በቦርዱ የሚሰጥ መሆኑን የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ይልቃል አስገንዝበዋል፡፡ ኮሚቴው ከንግዱ ማህበረሰብ፣ ከነባር የአካዳሚክ አባላት፣ ከሴኔት፣ ከተማሪዎች እንዲሁም ከቦርዱ አንድ አንድ ተወካይ የተዋቀረ እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል፡፡ የምርጫ ሂደቱ ግልጽነት ለማረጋገጥም ከአስተዳደር ሠራተኞች፣ ከመምህራን እና ከተማሪዎች ደግሞ የምርጫ ታዛቢዎች ተወክለው በምርጫው ሂደት ተሳትፈዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአስ/ተማ/ጉ/ም/ፕሬዚዳንት እጩ ተወዳዳሪዎች ዶ/ር ታፈረ መላኩ ከደ/ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ዶ/ር አነጋግረኝ ጋሻው ከወሎ ዩኒቨርሲቲ እና ዶ/ር ባመላኩ ታደሰ ከሐረሚያ ዩኒቨርሲቲ ቢሆኑም ዶ/ር ባምላኩ ታደሰ በምርጫ ወቅት በቦታው ባለመገኘቱ ለምርጫው ተሳታፊ አልሆነም፡፡ ስለሆነም ዶ/ር ታፈረ መላኩ እና ዶ/ር አነጋግረኝ ጋሻው እያንዳንዳቸው የምረጡኝ ቅስቀሳ መግለጫ አቅርበዋል፡፡ እጩ ተወዳዳሪዎች ያደረጉትን የምረጡኝ ቅስቀሳ ተከትሎም መራጮች ለምርጫ በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት የድምፅ መስጠት ፕሮግራሙ ተከናውኗል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ መጽሐፍትን በልገሳ አገኘ

በወርቅነሽ ደመም



በልገሳ የተገኙ መፅሐፍት ርክክብ ሲካሄድ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓት-ፆታ፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስ እና አካል ጉዳተኞች ዳይሬክቶሬት ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች 200 መጽሐፍትን በእርዳታ አገኘ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓት-ፆታ፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስ እና አካል ጉዳተኞች ዳይሬክቶሬት ዳይሮክተር የሆኑት ወ/ሮ የውልሰው መላክ ዩኒቨርሲቲው አዲስ ከመሆኑም አንፃር ለአካል ጉዳተኞችና ለሌሎች ተማሪዎች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና የተለያዩ ግብዓቶችን ለማሟላት የተለያዩ ድርጅቶች ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡ ምቹ ሁኔታዎች ከሚፈጠሩባቸው መንገዶች አንዱ ለአካል ጉዳተኞች የተለያዩ ግብዓቶችን ማሟላት ሲሆን ግብዓቶችን ለማሟላት ደግሞ ዳይሬክቶሬቱ ከተለያዩ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመፃፃፍ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ በመበተን ኮድ ኢትዮጵያ የሚባል ድርጅት በገንዘብ የሚተመኑ የተለያዩ ቁሳቁሶችን እንዲለግሱ ትብብር ሲጠይቁ እገዛ ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆን የቅርብ ጊዜ እትም

የሆኑትንና ለዩኒቨርሲቲው ይጠቅማሉ ተብለው የሚገመቱ 200 የተለያዩ መፅሐፍትን በእርዳታ ማግኘት እንደቻሉ ገልፀዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ዶ/ር በለጠ ያፅቆብ በበኩላቸው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የተለያዩ ቁሳቁሶች የተሟሉ ስላልሆኑ የሴቶች ጉዳይና ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ ዳይሬክቶሬት ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር እንደዚህ አይነት ድጋፍ እንዲገኝ የተደረገውን ጥረት በማመስገን ለወደፊትም ብዙ መርጃ መሣሪያዎች፣ መፅሐፍትና የመሳሰሉት ስለሚያስፈልጓቸው ከዚህ የበለጠ ሥራው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በመቀጠልም የቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ተወካይ ዳይሬክተር አቶ አዝመራው እንዳለ ቤተ መጽሐፍት በዋናነት የመማር ማስተማሩን ስራ ለማሳለጥ አስፈላጊ እንደሆነና መፅሐህፍትም የሚገኙት በግዥ፣ በልውውጥና በእርዳታ እንደሆነ በመጥቀስ የተገኙ መፃህፍት በተገቢው መንገድ ተደራጅተው ለተማሪዎች እንዲደርሱ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ በልገሳ የተገኙት መፅሐፍት በአብዛኛው የሶሻል ሳይንስ ሲሆኑ ጥቂቶች ደግሞ የተፈጥሮ ሳይንስ ናቸው፡፡

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በፓናል ውይይት አከበረ

በእንደሻው ያዛቸው



በ/ደ/ማ/ዩ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ማናየ ዓለሙ ለውይይቱ መነሻ ፅሑፍ ሲያቀርቡ

ደ/ማ/ዩ፡- “ራዕይ ሰንቀናል ለላቀ ድል ተነስተናል!” በሚል መሪ ቃል በአገር አቀፍ ደረጃ ለ10ኛ ጊዜ የሚከበረውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን ምክንያት በማድረግ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በዓሉን በፓናል ውይይት በደመቀ ሁኔታ አክብሮታል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

በዓሉ የተከበረው በፓናል ውይይት ሲሆን ለውይይቱ መነሻ ፅሑፍ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሆኑት በአቶ ማናየ ዓለሙ ቀር ቧል፡፡ በውይይቱም የሰንደቅ ዓላማ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የሰንደቅ ዓላማ ልማትና የሚያስተላልፉት ትርጉም በተለያዩ ጊዜያት ከነበሩት የመንግስት የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀም ጋር በማያያዝ ጽሁፉ ቀርቦ ውይይት ተደርጉበታል፡፡

የሠንደቅ ዓላማ አከባበር ሲነሳ የሀገሪቷን አንድነት፣ ሉዓላዊነት፣ የሀገር ፍቅር፣ የህብረተሠቡን ማንነት፣ ዕምነት፣ ወግ፣ ባህና ትውፊት የሚያንፀባርቅ ሠፊ አዉድ ያለው ይዘት በመሆኑ በልዩ እንክብካቤና ወኔ ሊያዝ እንደሚገባ ተጠቁሟል፡፡

የሠንደቅ ዓላማ ቀን መከበር ዜጐች በመተሳሰብ፣ በጋራ በመስራት፣ በኃላፊነትና በቅንነት የተጣለባቸውን ሀገራዊ አደራን በማሳደግ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ሊያጠናክሩበት የሚያስችል የዜጐች የብሄራዊ አንድነት መገለጫ አርማ መሆኑን ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡

በውይይቱም የቀድሞ ጀግኖች አባቶቻችን በድል፣ በሀዘን ፣ በደስታና በሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ባንዴራቸውን በማንገብ ለሀገራቸውና ለማንነታቸው ክብር የሞቱላት፣ የነፃነታቸው መገለጫ እንደነበር በማውሳት፣ የአሁኑ ትውልድም በፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ስርዓት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ፈርጀ ብዙ ተግዳሮችን በበሰለ አኳሃን በውይይት መፍታት እንደሚገባ ተነስቷል፡፡ ክብሯንም በደሙ ውስጥ ይዞ የሀገር ፍቅርን ተላብሶ የበለፀገች ሀገር መገንባት የወጣቱ ሚና መሆን መቻል እንዳለበት፣ ት/ቤቶችና ሌሎች ተቋማትም በዚህ ረገድ ጠንክረው መስራት እንዳለባቸውም ተነስቷል፡፡

በመጨረሻም ሁሉም ተሳታፊዎች ከመቀመጫቸው በመነሳት የኢትዮጵያን ህዝብ መዝሙር በክብር በመዘመር የፓናል ውይይቱ ፍፃሜ ሆኗል፡፡

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረመ

በእንደሻው ያዛቸው

**ደ/ማ/ዩ፡-** ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መማር ማስተማር፣ ምርምርና ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝር ጉዳዮችን ለመስራት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ በመሆን ጥቅምት 3/2010 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲው ሴኔት አዳራሽ የትብብር መድረክ በማካሄድ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ግንኙነትና ትብብር ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ሃይማኖት ዋሴ እንግዶችንና የፕሮግራሙን መርሃ ግብር ሲያስተዋውቁ እንደተናገሩት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከበርካታ የሀገርና የውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ማዕከላትና ኢንዱስትሪዎች ጋር የትብብርና አጋርነት ሥራ እየሠራ እንደሆነ ገልፀዋል፤ አወያይተዋል፤ በባለቤትነትም ሠርተዋል፡፡

የትስስር መድረኩ ዓላማ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2009 ዓ.ም. የተፈራረሙትን የትብብርና አጋርነት ሰነድ በዝርዝር የሚያይና ወሳኝ ሁነቶች ዙሪያ በጥልቀት ሊሠራ የሚያስችል እንደሆነ ዶ/ር ኃይማኖት ገልፀዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ታደሰ ጤናው ፕሮግራሙን ሲከፍቱ እንደተናገሩት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2ኛው ትውልድ የተመሠረተ የቅርብ ዩኒቨርሲቲ ቢሆንም በመማር ማስተማር፣ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎትና ሌሎች በርካታ ውጤታማ ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ከመማር ማስተማሩና ምርምሩ ጋር በተያያዘ በተቋም ደረጃ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በ2009 ዓ.ም. በትብብርና አጋርነት ስራዎችን በጋራ እየሠራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተለይም በጮቄ ተፋሰስ ዙሪያ የተሠሩ ሥራዎች እንዳሉም በመድረኩ አብራርተዋል፡፡ ስለሆነም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አንጋፋና ቀደምት ዩኒቨርስቲ በመሆኑ በቀጣይ በቅርበት ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ለመስራት እንዲቻል የተዘጋጀ የስምምነት መድረክ በመሆኑ ዝርዝር ሥራዎችን በጥልቀት ያካተተ እና ቋሚ ፕሮግራም የያዘ መድረክ ነው ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የስምምነቱ አባል የሆኑት ዶ/ር ካሳሁን ቱሬ በበኩላቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጥናትና ምርምር ስራ፣ ጥናትና ምርምርን ለማዳበር የአቅም ማጐልበቻ ስልጠና እና በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ በሚሉ ሶስት አበይት የትብብር መስኮች በጋራ እንደሚሠሩ ገልፀዋል፡፡ በተለይም በሕብረተሰብ ህይወት ዙሪያ የተጋረጡ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በሳይንሳዊ መንገድ በማጥናት የማህበረሰብ አገልግሎት እየሠሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ያለበት የምስራቅ ጐጃም ዞን የስድስቱ ስነ-ምህዳራዊ ቦታዎች ያሉበት ዕድለኛ አካባቢ በመሆኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጥምረት በአካባቢ ጥበቃ ትምህርት፣ ጥናትና ምርምር ስራ እና ስልጠና የመሣሠሉትን ነገሮች እንደሚሠሩ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በሁለቱ ተቋማት መካከል የጠበቀ ግንኙነት እየፈጠሩ የስራ ዝርዝሩን በዕቅድ አዘጋጅተው ወደ ተግባር የሚቀይሩ የግብረ ሃይል አባላትን ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች መርጠዋል፡፡ በዚህም ዶ/ር መስፍን አባተ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሰብሳቢ ሆኖ ሲመረጥ፣ ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና ዶ/ር ካሳሁን ቱሬ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አባል ሆነው ተመርጠዋል፡፡ የስምምነት ሠነድም ተፈራርመዋል፡፡

# የግብርና ኮሌጅ ከጃፓይጎ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ስልጠና ሰጠ

በእንደሻው ያዛቸው



ተሳታፊዎች ዉይይት ሲያደርጉ

ደ/ማ/ዩ፡- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከጃፓይጎ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር አሳታፊ ስርዓት ያታን ያማከለ የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴን ከጥቅምት 3-10/2010 ዓ.ም. በጉዛምን ሆቴል ስልጠና ሰጠ፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ዲን ወ/ሮ ወርቅነሽ ጥሩነህ ስልጠናው በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ ስር ለተቀጠሩ አዲስ፣ በዝውውር ለመጡና በሙያው ብዙ ቆይታ ለሌላቸው መምህራን ለትምህርት ጥራት የጐላ ሚና እንደሚኖረው ታስቦ ነው የተሰጠው፡፡

ስልጠናው የሚሠጠው ቀደም ብለው ስልጠናውን በወሰዱ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ መምህራንና ጃፓይጐ ኢትዮጵያ በተሰኘው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በጥምረት ሲሆን ጃፓይጐ ኢትዮጵያ አዳራሽ ተከራይቶ፣ ቁሳቁሶችንና ሌሎች የሎጅስቲክ አቅርቦቶችን በማሟላት እንደሆነ ወ/ሮ ወርቅነሽ አክለው ገልፀዋል፡፡

በጃፓይጐ-ኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት የትምህርትና ስልጠና አማካሪ አቶ መብት ከበደ በበኩላቸው ጃፓይጐ-ኢትዮጵያ ሴቭ ዘችልድረን/save the children / ከተሠኘ ድርጅት ጋር በጋራ በመሆን ግሮው ስሩ ኒወትሪሽን /Grow through nutrition/ የሚባል የ5 ዓመት /2016-2021/ የልማት ፕሮጀክት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ፕሮጀክቱ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የቅድመ ተግባር ትምህርት (Pre-service Education) በስርዓተ ትምህርት ማስፋፋት፣ በአቅም ማጐልበት ስልጠና፣ የአተገባበር ስነ-ዘዴን ማስፋፋትና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ እንደሚሠራ አቶ መብት ጨምረው ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ስልጠናው የመምህራንን አቅም በማጐልበት በትምህርት ጥራት ላይ አዎንታዊ እምርታን ለማምጣት እንዲቻል የመንግስት ስራን ለመደገፍ የሚሠራ ድርጅት በመሆኑ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም የእቅዳቸው አንድ አካል እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻም በየጊዜው የሚቀጠሩትንና ሌሎች ስልጠናውን ያልወሠዱ መምህራንን እየተከታተሉ ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ በመተባበር በትምህርት ጥራት ላይ የጐላ ስራ እንዲሠሩ አስተባባሪው ገልፀዋል፡፡

# የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ኤክስቴንሽን ተማሪዎች የጋራ መፀዳጃ ቤቶች ሰርተው አስረከቡ

በእንኘው ያዛቸው





ተማሪዎች ያሰሩት መፀዳጃ ቤት ሲጎበኝ

ደ/ማ/ዩ፡- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የኤክስቴንሽን ተማሪዎች በደብረ ማርቆስ ከተማ በ3 ቦታዎች ላይ የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን ሰርተው አስረከቡ፡፡

ተመራቂዎች ወደ ህብረተሰቡ በሚገቡበት ጊዜ ከህብረተሠቡ ጋር በቀላሉ ተግባብተው በማህበረሰቡ ውስጥ የተጋረጡትን ችግሮች በመለየትና ሳይንሳዊ ዘዴን ተጠቅመው ቅድሚያ በመስጠት ወደ ተግባር መግባት አንዱ የትምህርታቸው አካል እንደሆነ በመገንዘብ፣ የቤት ለቤት



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የጤና አገልግሎትን ለማሻሻል ግንዛቤ መፍጠር እና ሌሎች ተግባራትን መስራት እንደቻሉ ተማሪዎች ገልጧል ፡፡

በስራቸው ወቅት በርካታ ፈተናዎች ቢገጥሟቸውም ጥሩ የተግባቦት መንፈስ በመፍጠር አንድነታቸውን ያጠናከሩበት፣ የቡድን ስራን ያሰፈኑበት ብሎም የህብረተሠቡን ችግር ለመቅረፍ ከህብረተሰቡ ጋር ተግባብተው መስራት የቻሉበት በድልም ኃላፊነታቸውን የተወጡበት እንደነበረ ተማሪዎች አስረድተዋል፡፡

በዚህም ረገድ በአየር ማረፊያና አካባቢው ለአሽከርካሪዎች፣ ለቆሎ ተማሪዎች ለግቢ ተማሪዎችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ሁለት ሽንት ቤት ሰርተው አስረክበዋል፡፡ በቀበሌ 03 ደግሞ ለገበያተኛው የጋራ መጠቀሚያ የሚያገለግል ያስጀመሩት የጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ከቀበሌዎች፣ ከአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ከመንቆረር ኢንተርፕራይዝ /ኮንስትራክሽን/፣ ከአልማና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮጀክቶች መሰራታቸውን ተማሪዎች አብራርተዋል፡፡ በቀጣይም አዲስ የሚመደቡ የግልና የመንግስት ተማሪዎች የተጀመረውን የፕሮጀክት ስራ አጠናክረው በመስራት ከፍፃሜ እንዲያደርሱት ተመራቂ ተማሪዎች አሣስበዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ከፍተኛ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳይ ምክትል ፕሬዚዳንት የሆኑት አቶ ታደሰ ጤናው እና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንት ረዳት ፕሮፌሰር ገነት ደጉ ተማሪዎች ወደ ህብረተሰቡ ገብተው ስራቸውን በሚሠሩበት ጊዜ በርካታ ፈተና እንደገጠማቸውና በከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ችግሮችን መፍታት እንደቻሉ ልምድም እንዳገኙበት ገልፀዋል፡፡ ይህ ለቀጣይ ከማህበረሰቡ ጋር ለሚሠሩት ሥራቸው የተሻለ አጋጣሚ እንደፈጠረላቸው ገልፀዋል፡፡ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በተቻለው አቅም ሁሉ እንደሚያግዝ አስረድተዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን አቶ ዱቤ ጃራ በበኩላቸው የጤና ሳይንስ ኤክስቴንሽን ተማሪዎች በፅንሰ-ሃሳብ ደረጃ የተማሩትን እውቀት ወደ ማህበረሰቡ ሲገቡ በምን መልኩ መተግበር እንዳለባቸው የሚያሳይ የተግባር ትምህርት ሰርቶ ማሳያ ነው፡፡ ዓላማውም ተማሪዎች በሚመደቡበት ቦታ ሁሉ የሚገጥሟቸውን ችግሮች በቀላሉ ተረድተው ከመለየት ጀምሮ ህክምና እስከመስጠት ድረስ ያለውን ሂደት በእውቀት ላይ የተመሠረተ ስራ እንደሠሩ ማስቻል ነው ብለዋል፡፡ በቀጣይም እነዚህን ተግባራት ዩኒቨርሲቲው በፕሮጀክት ቀረፆ መምህራን የሚገቡበት ሁኔታ ይመቻቻል ሲሉም አብራርተዋል ፡፡

በደብረ ማርቆስ ከተማ የቀበሌ 07 ምክትል አስተዳደር አቶ መከተ ተመስገን በጉብኝቱ ወቅት እንደተናገሩት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአካባቢያችን መፀዳጃ ቤት የህብረተሰቡ አንገብጋቢ ችግር መሆኑን ለይተው ችግሩን ለመቅረፍ በቀበሌ በሠሯቸው ተግባርም ተቀጥረው በሚሄድበት አካባቢ መልካም ስራ እንደሚሠሩ አመላካች ተግባር በመሆኑ ሊያስቀጥሉት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲውም ከጐናቸው ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ጤና ጣቢያዎች የተበላሹ የማሽን ጥገና ስራዎችን በመስራት ከፍተኛ ወጭ የሚገመት ገንዘብም አድነዋል፡፡

# ለአዳዲስ መምህራን ስልጠና /Induction Training/ ተሰጠ

*በስማቸው አየነው*





የስልጠናው ከፊል ገፅታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሰው ሀብት ልማት ስልጠና የስራ ክፍል አስተባባሪነት በዩኒቨርሲቲው አዲስ ለተቀጠሩ 34 መምህራን ከጥቅምት 14-17/2010 ዓ.ም ስልጠና ተሰጠ፡፡

የስልጠናው አስተበባሪ የሆኑት አቶ መላኩ ጥላሁን እንደገለጹት በቅጥር ወይም በዝውውር ምክንያት ዩኒቨርሲቲውን በአዲስ ለሚቀላቀሉ መምህራን የስራ ትውውቅ ስልጠና በየአመቱ እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡ በዚህም ወቅት ለአዲስ መምህራን የተሰጠው ስልጠናም የዚህ አካል ሲሆን ዩኒቨርሲቲውን በአዲስ የተቀላቀሉት መምህራን ለመማር ማስተማሩ ስራ አዲስ እንዳይሆኑ እና ለዩኒቨርሲቲው ራዕይና ተልዕኮ መሳካት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዲችሉ የስራ ትውውቅ ስልጠና/ Induction Training/ በመስጠት ወደ ስራ ማስገባት አስፈላጊ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

የስልጠና ዋና አላማ የመምህራንን አቅም በማሳደግ የመማር ማስተማሩን ስራ ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወን እንዲችሉ ማድረግ በመሆኑ የምዘናና ግምገማ ስርዓት፣ የክፍል አያያዝ፣ አሳታፊ የማስተማር ስነ ዘዴ፣ የዩኒቨርሲቲው ህግና ደንቦች እንዲሁም ስርዓተ-ፆታና ኤች አይቪ/ ኤድስ የሚሉ ርዕሶችን ያካተተ ስልጠና እንደተሰጠ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቀጣይም ሌሎች ስልጠናዎችን በማዘጋጀት መምህራንን ማብቃትና አቅማቸውን የማጎልበት ስራ የሚሰራ መሆኑን አስተባባሪዉ አክለዉ ገልፀዋል፡፡

አስተያየት የሰጡት የስልጠናው ተሳታፊዎች በበኩላቸው የተሰጠው ስልጠና በተደራጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ የተሰጠ ስለሆነ በጣም ጥሩ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በተለይ ልምድ የሌላቸዉ መምህራን ልምድ ካላቸው መምህራን ልምድ ማግኘት በማግኘታቸዉ ወደፊት በስራቸዉ ላይ በመተግበር የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ እንደሚችሉ ገለፀዋል፡፡

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ሃገር አቀፍ ግምገማዊ ስልጠና ሰጠ

በወርቅነሽደመም



የውይይቱ ከፊል ገፅታ

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2010 ዓ.ም. ብቁና ሀገር ተረካቢ ዜጋን በማፍራት ሥራ ውጤታማ እንዲሆን በተለያዩ አርዕስቶች ዙሪያ በዋናው ግቢና በቡሬ ካምፓስ የተማሪዎች ግምገማዊ ስልጠና አካሄደ፡፡ የውይይቱ አላማም ዩኒቨርሲቲው ብቁና ሀገር ተረካቢ ዜጋን ለማፍራትና ውጤታማ አሰራርን ለማጎልበት ተማሪዎች እንዴት አቅደው መስራት እንዳለባቸው፣ ምን ምን ፈተናዎች እንዳሉና የላቀ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችሉ አሰራሮችን ለማስገንዘብ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ስልጠናው ሴኩራሊዝምና

የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ያለውን ገጽታ ግንዛቤ ለማስያዝ እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ለነባርና ለአዲስ መደበኛ ተማሪዎች የውጤታማነት ስኬት አሰራር ሥርዓትን (Deliverology) ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ የማስፈፀሚያ ስልትና የባለድርሻዎች ሚና ምን እንደሚመስል በሰፊው ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ የሥነ ዜጋና የሥነ-ምግባር ትምህርት ስኬቶች፣ ክፍተቶችና ቀጣይ አቅጣጫዎች ምን እንደሆኑ እና በጥልቅ ተሃድሶ ወቅት የተለዩ ችግሮች፣ የተቀየረው ሁኔታና ቀሪ ስራዎችን በተመለከተም በዩኒቨርሲቲው መምህራን የመወያያ ጽሑፉ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

ከዚህ በመቀጠልም ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸው ምን ያህል እንዳወቁ ለመገምገም የሚፈተኑትን ማጠቃለያ ፈተና (Comprehensive exit exam) በተመለከተም ገለፃ ተደርጎላቸዋል፡፡

ለአዲስ ተማሪዎችም በተለየ መልኩ ስለሴኩላሪዝም ምንነትና የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ያለውን ገጽታ በተመለከተ ጽሁፉ በሚመለከታቸው አካላት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጐበታል፡፡ በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው የ2009 ዓ.ም. አፈፃፀም እና የ2010 ዓ.ም. ዕቅድም ለነባርና አዲስ ተማሪዎች ቀርቦ ውይይት ተደርጓል፡፡ ከውይይቱ በኋላም የተለያዩ ጥያቄዎች በተማሪዎች ተነስተው በሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ተሰጥባቸዋል፡፡

ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን በተለያዩ ፕሮግራሞች እየሰጠ ሲሆን ከመደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ አዲስ ለሚገቡ የማታ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ የዩኒቨርሲቲውን ህጎችንና ደንቦችን በተመለከተ ገለፃ በማድረግ የቅድመ ትውውቅ ስራ ሰርቷል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# በቡሬ ካምፓስ ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጠ

በስማቸው አየነው



የስልጠናው ክፊል ገፅታ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በቡሬ ካምፓስ በ2010 ዓ.ም ትምህርታቸውን ለመከታተል ተመድበው ለገቡ 500 አካባቢ አዲስ ተማሪዎች የሁለት ቀን የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጠ፡፡

የህይወት ክህሎት ስልጠናውን የሰጡት አሰልጣኝ መምህራን እንደገለፁት ስልጠናው ለሁሉም የግቢው ማህበረሰብ መሰጠት ያለበት ቢሆንም የጊዜ እና የስልጠና ቦታ እጥረት በመኖሩ በዚህ አመት ከተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ትምህርታቸውን ለመከታተል ለመጡ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ብቻ እንዲሰጥ ተደርጓል ብለዋል፡፡ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ በመሆኑ የተለያዩ የአኗኗር፣ ባህሪያት እና አመለካከት ችግሮች ስለሚገጥሟቸው እንዲሁም ከዚህ በፊት በቤተሰቦቻቸው ኃላፊነት ሲመሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ግቢ ሲመጡ ራሳቸውን ችለው መኖርና መምራት ሲጀምሩ ልዩ ልዩ ችግሮች ስለሚገጥማቸው የህይወት ክህሎት ስልጠና በመስጠት የሚገጥሟቸውን ችግሮች በመቋቋም ሳይንሳዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ፣ የራስ መተማመን መንፈስ በተሞላበትና በተረጋጋ መንፈስ ውሳኔ በማሳለፍ የመጡበትን አላማ ለማሳካት እንዲችሉ ለማድረግ ስላስፈለገ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም የዚህ ስልጠና ፋይዳ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው አሉታዊ የአቻ ግፊትን በመቋቋም ጠቃሚና ጎጅ ባህሪያትንና ድርጊቶችን በመለየትና በመቋቋም ውጤታማ ሆነው እንዲወጡ ያስችላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በአጭር ጊዜም ቢሆን መሰረታዊ የሆነውን የህይወት ክህሎት ስልጠና መስጠት ተችሏል ብለዋል፡፡



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

ስልጠናውን የተካፈሉ ተማሪዎች በበኩላቸው የዚህ አይነት ስልጠና መሰጠቱ ከቤተሰብና አካባቢያችን ተለይተን ግቢ ስንገባ ከዚህ በፊት ያልለመድናቸው በርካታ አዲስ የሆኑ ባህሪያት እና ችግሮች ለምሳሌ እንደ ደባል ሱስ፣ ጊዜን ማባከን፣ የአቻን ግፊት አለመቋቋም፣ ራስን ማስጨነቅና መሰል ችግሮች ሊያጋጥሙን ስለሚችሉ ከማናቸውም አሉታዊ የአቻ ግፊት ነፃ ሆነን መቋቋም እንድንችል እና በራስ መተማመን መንፈሳችንን በማሳደግ የመጣንበትን አላማ ለማሳካት ያገለግለናል፡፡ በተለይም ደግሞ ሴት ተማሪዎች ለፆታዊ ትንኮሳ እና አቻ ግፊት ከወንዶች የበለጠ ተጋላጭ ስለሆንን ከዚህ ችግር ራሳችንን መጠበቅ ያስችለናል በማለት ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም በዚህ ስልጠና ብቻ ሁሉንም ችግሮቻችን መቅረፍ ስለማይቻል የስርዓተ ፆታ እና መሰል ክበባት ተቋቁመው ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራው እንዲቀጥል አሳስበዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ቡሬ ካምፓስ የሴቶች፣ ኤች አይቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች አስተባባሪ የሆኑት ወ/ሮ አዘበብ በላይ የህይወት ክህሎት ስልጠናው ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች መሰጠቱ የተማሪዎችን በራስ መተማመን መንፈስን ለማሳደግ፣ ለልዩ ልዩ ማህበራዊና የጤና ችግሮች እንዳይጋለጡ ለማድረግ በማሰብ ሲሆን በቀጣይም ልዩ ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ውጤታማ መሆን እንዲችሉ እንደሚሰራ አስገንዝበዋል፡፡

**የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መፅሔት ደንበኛ መሆን ከፈለጉ በዩኒቨርሲቲው የህዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በመምጣት ማግኘት ትችላላችሁ፡፡**



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

# Haddis Alemayehu Cultural Study Institute Conducts Proposal Defense



DMU:- Haddis Alemayehu Cultural Study institute hold proposal defense on different research thematic areas on October 27/2017.

The director of Haddis Alemayehu Cultural Study Institute Mr. Gizachew Andarge, states that doing proposal defense is one among the part and parcel of the mission of the institute that it usually does. For that matter, different researchers from different disciplines and experts have presented their proposal individually and in groups.

Thus, Assessing the attention and values given to culture as foundation and dimension of development, archaeological investigation in the edge of Abay Gorgi focus on Melkie Cave; Assessing the indigenous knowledge Scientifically: the case of Eastern Gojjam zone; usage of Amharic naming words in elementary school science government schools and culture and technology in the Jibela Motera mount during imperial region were the proposals topics reflected.

During the presentation, several questions and constructive comments were raised rationally and the presenters and other members provided their genuine explanations. During the occasion it was noted that the proposals presented by different scholars and research experts emphasize, announce and transfer for generations from time to time of the cultures as well the total achievements of the people in the locality incredibly.

# Debre Markos University Establishes Partnership with Addis Ababa University

DMU: - Debre Markos University has conducted collaboration and partnership with Addis Ababa University to carry out activities on teaching learning, research, well-informed and demanded community service and other supplementary tasks to work mutually on October 3, 2017 in the university senate room.

Debre Markos University foreign relation and partnership coordinator Dr. Haimanot Wassie states that the collaboration has been started since 2016 and, and currently are enable to oversee the details of the tasks of the two universities cooperatively in profoundly.

According to Dr. Haimanot explanations Debre Markos University has conducted partnership with several local and foreign institutions, and thence cooperates and leads the discussions intellectually.

Debre Markos University Academic Affairs Vice President Mr. Tadesse Tenaw, officially states that Debre Markos University has been carrying out adequate and efficient activities on teaching learning, research, community service and other additional deeds incredibly in spite of its establishment recently as a 2$^{nd}$ generation University. Therefore, it is a great fortune to leave fertile opportunity to share experiences between Debre Markos University and the popular Addis Ababa University to work mutually in proxy manner, Mr. Tadesse added.

Thus, Debre Markos University and Addis Ababa University have begun their holistic relation to perform activities on teaching learning, research and other additional tasks institutionally since 2016. However, their potential in depth has not yet harnessed. For that matter, the two universities have ratified detailed descriptions to perform admirable activities tangible especially on the slightly began Choke watershed area.

Dr. Kasahun Turie, Addis Ababa University instructor, on the other hand explains that Addis Ababa University has passed through several research activities, schooling on environmental protection and preservation and offered



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

demanded skill- gap trainings on how to conduct researcher accordingly. Especially, tap-rooted problems in the community have been scientifically solved, Dr. Kassahun added.

Fortunately, Eastern Gojjam Zone where Debre Markos University is located is naturally endowed with the existence of the six climatic zones; (hot biodiversity area) should do problem solver research with Addis Ababa University cooperatively. Strong keen leaders have been chosen from the two universities to sustain the partnership strongly designing detailed working plans. During the MoU signing program taskforce was organized to execute the Mou Agreements. In due course of this, Dr. Mesfin Abate from Debre Markos University as a chairman, assistance professor Genet Degu from Debre Markos University and Dr. Kassahun Turie from Addis Ababa University respectively are chosen as members of the partnership taskforce.

# Debre Markos University has got books via Donation



DMU: Debre Markos University Gender Affairs and HIV/AIDS prevention directorate has got 200 books from various non-governmental organizations /NGOs/. The director of Debre Markos University Gender Affairs and HIV/AIDS prevention directorate Mrs. Yewulsew Melak states that Debre Markos University usually enquires different institutions so as to create hospitable and fertile environment for students in general and disabled students in particular. Fulfilling ample inputs from governmental and nongovernmental organizations is an instance that the university goes further discoursing projects. In doing so, the university has got 200 different new edition books in different disciplines from “code Ethiopia”:(None governmental organizations /NGOs/) institution through donations.

During the tender programme, Dr. Belete Yaecob, Debre Markos University Academic Executive Director on his turn explains as Debre Markos University is a recently opened university. There are inadequate infrastructures and inputs employed for



09-13-88-63-49 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 dmu.cc2008@gmail.com Website: www.dmu.edu.et

disabled students. Thus, Debre Markos University Gender affairs and HIV/AIDS directorate has been offered philanthropic support from different institutions through negotiating and addressing restless endeavors especially books.

The Acting director of Debre Markos University Library and documentation service directorate Mr. Azimeraw Andualem, on his turn strongly acknowledged the donation that they received. Also, the books would have sound importance from improving the teaching- learning process and therefore the books could certainly be shelved and accessible to the students.

Eventually, Mrs. Yewulsew Melak remarked as the books have been outsourced through strong diplomatic efforts though the books are more of social streams; it minimizes the problems faced slightly.

# Debre Markos University College of Agriculture Gives Training in association with Jhpiego





DMU:- Debre Markos University in cooperation with Jhpiego Ethiopia offer competency –based gender responsive pedagogy training from October 10-17/2017 in Gozamin Hotel, Debre Markos Town.

The dean of Debre Markos University college of Agriculture W/ro Workinesh Tirunenh states that the training has given to the newly employed, transferred and non trained teachers. Hence, this could have vital significances to bring quality education in general and consider gender concerns in planning the lessons in particular.

It was also noted that the gender responsive pedagogy training pay attention for both male and females to the learning teaching activities to make the classroom practices largely on gender-based, avoid gender-biased, stereotypes and finally so as to make the innovative learning approaches even more gender sensitive though interactive learning methodology. Therefore, the innovative approaches of teaching- learning could lastly meet its climax and targeted learning outcomes, she added.

According to Mr. Mebit Kebede, from Jhpiego- Ethiopia None governmental organizations education and training consultancy, on his turn explains that Jhpiego Ethiopia has been working cooperatively with save the children on the project entitled “Grow through nutrition” for the coming five years /2016-2021/ the training could be able to elevate the teachers intellect to perform their plan on their work in their university they working.